# በመቃብራችሁ ድል ይረጋገጣል

(ከእኔ ዓለም)

ያደወርሽው ድውር ጥምጥሙ በዛና
ያናውጥሽ ጀመር እግሩ ቀጠነና
ባፍጢምሽ ሳይደፋሽ መቼ ይቆማልና።

የረዥም ዘመንን ታሪክን ክዳችሁ
ያገር ሕልውናን ክፍፍል ይዛችሁ
ኢትዮጵያዊ ክብርን ረጋገጣችሁ
አገርን ቆርሳችሁ ሕዝብን የለያችሁ
ያ አልበቃ ብሎ ወሰን አሳልፎ ድንበር የሰጣችሁ
ለም መሬታችንን ለውጭ የሸጣችሁ
ወገንን በንቀት ያበሻቀጣችሁ
ሕዝብ በገዛ አገሩ መብት የቀማችሁ
ቅርስ ሃብት ንብረቱን የዘረፋችሁ
ሰንደቅ ዓላማዋን ጨርቅ ነው ያላችሁ

በዘር በሃይማኖት እያናቆራችሁ
ደም በደም ተነክሮ እግርና እጃችሁ
የሕዝብ ድምጽ ሰርቆ መረጠን ያላችሁ
በድሃው ወገኔ ደም የታጠባችሁ
የበደል እሮሮ በንቀት ያያችሁ
ፍትሕ በጠየቀ ሞት የፈረዳችሁ
እግር እጅ የፊጢኝ ቶርች ያሰቃያችሁ
በሚስጢር በድብቅ ደም አፈሰሳችሁ
ህፃን ወጣት ሳይቀር በጥይት ቆላችሁ

የሰራችሁት ግፍ አንቆ ሊውጣችሁ

ማጥ ውስጥ ገብታችሁ ከነ ወንጀላችሁ
የከረማችሁት በደም ተጠምቃችሁ

ትዕግስትና እርጋታን ፍርሃት ያላችሁ
ደም ጕርሶ ይወጣል በቀል ነው ምሳችሁ
ሰዓቱ ደረሰ አለቀ ቀናችሁ
ሕዝብ ተቆጥቷል አምርሮ ተነስቷል
አንድነት ሕብረቱን ኃይልን አስተባብሯል
ለፍፃሜነቱ ሁሉንም ያደርጋል
በእናንተ መቃብር ላይ ድል ይረጋገጣል።